ቀን: ________________

# የውክልና ሥልጣን

ወካይ: ________________
ዜግነት: ________________
የፓስፖርት/መታወቂያ ቁ. ________________
የመኖሪያ አድራሻ: ________________
________________

ተወካይ: ________________
ዜግነት: ________________
አድራሻ: ________________
________________

እኔ ወካይ ለተወካይ የምሰጣቸው የውክልና ስልጣን በስሜ የተመዘገበውንና ወደፊት በስሜ የሚመዘገበውን የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት እንዲጠብቁ፣ እንዲቆጣጠሩ፣ እንዲያስተዳድሩ፣ እንዲያከራዩ፣ እንዲያኮናትሩ፣ የኪራይም ሆነ የኮንትራት ገንዘብ እንዲቀበሉ፣ እንዲሸጡ፣ እንዲለውጡ፣ ውል እንዲዋዋሉ፣ ስም እንዲያዛውሩ፣ ገንዘብ በቼክም ሆነ በጥሬ ገንዘብ ተሳስበው ሰነድ ፈርመው እንዲቀበሉ፣ በስሜ የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት እንዲገዙልኝ፣ ስሙን በስሜ እንዲያዛውሩ፣ በስሜ በማህበር ተደራጅተው በሊዝ፣ በጨረታ፣ ቦታ በመመራት ለመኖሪያ ቦታ እንዲረከቡ፣ የግንባታ ፈቃድ እንዲያወጡ፣ የግንባታ ስራ እንዲያሰሩ፣ ለግንባታ የሚያስፈልጉ ማቴርያሎችን እና ሲሚንቶ እንዲገዙ፣ በስሜ ካርታ ፕላን፣ የባለቤትነት ማስረጃ ደብተር፣ ሊብሬ እንዲያወጡ፣ የፕላን ማሻሻያ አሰርተው እንዲቀበሉ፣ በስሜ ሰሌዳ እንዲያስቀይሩ፣ አመታዊ የተሽሽከርካሪ ግብር ከፍለው ቦሎ ከላውዶ እንዲያስደርጉ፣ የመንጃ ፈቃድ እንዲያሳድሱ፣ የነዋሪነት መታወቂያ እንዲያሳድሱ፣ ውሃ፣ መብራት፣ ስልክ እንዲያስገቡ፣ በስሜ የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲያወጡ፣ በስሜ የንግድ ፈቃድ እንዲያወጡ፣ እንዲያድሱ፣ የንግድ ዘርፉን እንዲቀይሩ፣ አስፈላጊም ሲሆን ተመላሽ እንዲያደርጉ፣ ግብር እንዲገብሩ፣ የሚከፈሉ ክፍያዎችን እንዲከፍሉ፣ ሰነድ ላይ እንዲፈርሙ፣ ሰነድ እንዲቀበሉ፣ በስሜ ጨረታ እንዲጫረቱ፣ ውል እንዲዋዋሉ፣ በጨረታ ያሸነፉትን ማንኛውንም ንብረት እንዲረከቡ፣ ከጨረታ ተመላሽ የሚሆን ገንዘብ በቼክም ሆነ በጥሬ ገንዘብ ተሳስበው እንዲቀበሉ፣ በስሜ ሲ.ዔ.ዲ እና ኤልሲ. እንዲከፍቱ፣ በስሜ አዲስ የባንክ ሂሳብ እንዲከፍቱ፣ በስሜ በማንኛውም ባንክ ያለውን ገንዘብ እንዲያወጡ፣ እንዲያንቀሳቅሱ፣ ቼክ ለመመንዘር፣ ፈርመው ለመቀበል፣ ለመስጠት እንዲችሉ፣ በስሜ ሲፒኦ እንዲያሰሩ፣ በስሜ አክሲዮን እንዲያቋቁሙ፣ ድምጽ እንዲሰጡ፣ በስብሰባዎች ላይ እንዲገኙ፣ በመተዳደሪያ እና በመመስረቻ ደንብ ላይ እንዲፈርሙ፣ የአክሲዮን ድርሻዬን እንዲሸጡ፣ እንዲለውጡ፣ በቃለ ጉባኤ ሰነድ ላይ እንዲፈርሙ፣ አክሲዮን እንዲገዙ፣ በስሜ ከውጭ አገር የሚመጣውን እቃም ሆነ መኪና አስፈላጊው የጉምሩክ ፎርማሊቲ በማሟላት ለመረከብ እንዲችሉ፣ በውርስ ሆነ በስጦታ የማገኘውን የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት እንዲቀበሉ፣ ስሙን በስሜ እንዲያዛውሩ፣ የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረቴን በዋስትና በማስያዝ ከባንክ፣ ከግለሰብ፣ ከአበዳሪ ድርጅት ለመበደር እንዲችሉ፣ ተሳስበው እንዲከፍሉ፣ በባንክ ቤትም ሆነ በፖስታ አገልግሎት በስሜ የሚመጣውን ማንኛውንም እቃም ሆነ ሰነዶችን፣ የአደራ ደብዳቤ እንደኔ ሆነው ሰነድ ላይ ፈርመው እንዲረከቡ፣ በስሜ ኮንዶሚንየም ማህበር ተደራጅተው የመኖርያ ቤት እንዲረከቡ፣ ከመንግስት አካልም ሆነ ከግለሰብ እንዲሁም ከግል ድርጅት ማግኘት የሚገባኝን ማንኛውንም ገንዘብ ሆነ ጥቅማ ጥቅም አስፈላጊውን ፎርማሊቲ አሟልተው እንዲቀበሉ፣ በውርስ የማገኘውን የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ድርሻ ንብረት እንዲሸጡ፣ እንዲለውጡ፣ ውል እንዲዋዋሉ፣ ስም እንዲያዛውሩ፣ የድርሻ መልቀቅ ውል ስምምነት እንዲዋዋሉ፣ ድርሻ እንዲለቁ፣ እንዲቀበሉ፣ በአጠቃላይ በህዝባዊም ሆነ መንግስታዊ ድርጅት፣ በኤምባሲና ቆንስላዎች፣ በአስተዳደር መ/ቤት፣ በኢሚግሬሽን፣ በሥራና ከተማ ልማት፣ በቀበሌ፣ በክፍለ ከተማ መስተዳደር፣ በኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ኮርፖሬሽን፣ በኢትዮጵያ መብራት ሀይል ኮርፖሬሽን፣ በውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ድርጅት፣ በመንገድ ትራንስፖርት፣ በፖስታ ቤት እና ጉዳዬን በሚመለከተው በማንኛውም መ/ቤት እየቀረቡ እኔ መፈጸም የሚገባኝን ማንኛውንም ጉዳይ ተከታትለው እንዲፈጽሙና እንዲያስፈጽሙ፣ ኢንሹራንስ እንዲገቡ፣ ከኢንሹራንስ ጋር ውል እንዲዋዋሉ፣ የኢንሹራንስ ካሳ ገንዘብ እንዲቀበሉ፣ በምከሰስበትም ሆነ በምከስበት ጉዳይ በማናቸውም ፍ/ቤት ቢችሉ እራሳቸው ከአቅም በላይ ከሆነ የሕግ ጠበቃ ወክለው እንዲከራከሩ፣ መልስ እንዲሰጡ በቃለ መሐላ እንዲያረጋግጡ፣ ውሣኔ እንዲቀበሉ፣ ሌላ 3ኛ ወገን መወከልም ሆነ መሻር እንዲችሉ ይህንን ሙሉ የውክልና ሥልጣን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2199፣ 2205 እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 58 መሠረት የወከልኳቸው መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ::

የወካይ ፊርማ ________________